**አሰራርና አደረጃጀትን በተመለከተ**

ተቋሙ ሲመሰረት ሰልጠና የመስጠትና የማስተባበር፣ጥናትና ምርምር እና የምክር አገልግሎት የሚሰጥ ማዕከል ቢሆንም ተቋሙ ግን እነዚህን ተግባሮች ለመስጠት ምቹ ሁኔታ ያለመኖር፣ የአገልግሎት መስጫ ፋስሊቲዎች ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆን እንደ ቁልፍ ችግር ሁኖ ቆይቷል።ተቋሙ የምርምርና የምክር አገልግሎት መስጠት ሳይችል ሥልጠና በመስጠትና በማስተባበር ዙሪያ ብቻ ተገድቦ ቆይቷል። በጥናትና ምርምር እና በምክር አገልግሎት ለመስጠት አደረጃጀቱም ምቹ ሆኖ አልተገኘም ነበር። በመሆኑም ተቋሙ የተሰጠዉን ተልዕኮ ለማሳካት የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ፣ግልጽና ተጠያቂነት ለማድረግ አሰራርን ሊያሻሽሉ የሚችሉ የሲቭል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በምስረታ ዘመኑ እና ከተመሰረተ ቡላም ለጥቂት አመታት ከነበረው በተሻለ መልኩ ተግባራዊ በማድረግ የአሰራር ስርዓቶችን ለመዘርጋት ተችሏል። ከነዚህ መካከል መሰረታዊ የስራ ሂደት ለዉጥ(በክህሎት እና በአመለካከት የተሻሉ

አማካሪዎችን ወደ ተቋሙ እንዲገቡ በማድረግ)፣ የቢሮ ካይዘን እና የዉጤት ተኮር ስርዓት እንዲሁም ሌሎች የአሰራር ስረዓቶችን በመዘረጋቱ እና ተግባራዊ በማድረጉ በአመራርና ሰራተኞች ላይ የስራ መነሳሳትን በመፍጠር ተቋሙ በምስረታ ዘመኑ ወቅት እና ከምስረታ ወዲህም ለጥቂት ዓመታት የነበሩበትን ችግሮች ባለፉት ጥቂት አመታት ግን ከመቼዉም ጊዜ በበለጠ መልኩ ተልዕኮዉን እንዲወጣ የሚያስችለዉ መሠረት ላይ እንዲገኝ ዘረፈ-ብዙ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።በተጨማሪም ስራዎችን በጥራት ለማከናወን የሚጠቅሙ የተለያዩ መመሪያዎችና ማኑዋሎች በማዘጋጀት ምቹ የስራ አከባቢ ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ ይገኛል። ሆኖም አሁንም ከሌሎች ክልሎች አቻ ተቋማ አደረጃጀትና አሠራር አንፃር ሲታይ እንደገና አደረጃጀቱንና አሠራሩን በመፈተሽ የወቅቱ ልማት የሚጠይቀዉን አቅም መሸከም እና ፈጣን ምላሽ በመሰጠት በህዝቡ ሙሉ ተሳትፎ ፈጣንና ቀጣይነት ያለዉ ዕድገት በማረጋገጥ ለህዝብ ተጠቃሚነት የሚተጋ አመራርና ፈፃሚ ሀይል በብዛትን በብቃት የሚያበቃ ተቋም ለማድረግ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል።